# ቋሚ የወሊድ መቆጣጠሪያ (ማምከን)

| | **የቱባል ዘዴዎች ("ቱባል" ወይም "ቱቦዎችን ማሰር")**<br>**እነዚህ ዘዴዎች የፋሎፒያን ቱቦች (የማህፀን ቱቦ) በመዝጋት ወይም በመቁረጥ እንቁላል ከስፐርም እንዳይገናኝ ያደርጋሉ ሃኪሞች ይህን ማድረግ የሚችሉባቸው ጥቂት መንገዶች አሉ።** | **ቫሴክቶሚ**<br>**ይህ ዘዴ የወንድ የዘር ፍሬን ከወንድ ብልት ውስጥ እንዳይወጣ ይከላከላል።** |
|---|---|---|
| **እንዴት ነው የሚሰራው?** | ሐኪሙ በሆድዎ በኩል ወደ ቱቦዎች ይደርሳል። ከዚያም ማሰሪያ ባንዶች ወይም መቆንጠጫዎች በቱቦው ላይ ይደረጋሉ፣ ወይም የእያንዳንዱ ቱቦ ቁራጭ ይወገዳል። | ይህ ዘዴ የሚሠራው የወንድ የዘር ፍሬን በሚይዘው የዘር ከረጢት ውስጥ ያለውን ገመድ በመቁረጥ ነው። |
| **ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ ይሠራል?** | 98%፣ እንደ ዘዴው ይለያያል | > 99% |
| **ምን ያህል ያስከፍላል?** | በአብዛኛዎቹ የኢንሹራንስ ዕቅዶች እና በሜዲኬይድ ይሸፈናል (ዕድሜ ከ21 ዓመት በላይ ከሆነ)።<br><br>ካልተሸፈነ፣ ከ1,500 እስከ 6,000 ዶላር ያስከፍላል። | በአብዛኛዎቹ የኢንሹራንስ ዕቅዶች እና በሜዲኬይድ ይሸፈናል፡ በሜዲኬር አይሸፈንም።<br><br>ካልተሸፈነ፣ ከ350 እስከ 1,000 ዶላር ያስከፍላል። |
| **መታወቅ ያለባቸው ነገሮች** | እነዚህ ዘዴዎች እርግዝናን በቋሚነት ይከላከላሉ፣ እርግዝናን በመከላከል ደግሞ በጣም ውጤታማ ናቸው።<br><br>አንዳንድ ዘዴዎች ከወለዱ በኋላ ወዲያውኑ ሊደረጉ ይችላሉ።<br><br>ወድያውኑ ይሰራል።<br><br>ከኤችአይቪ እና ከሌሎች የአባላዘር በሽታዎች አይከላከልም።<br><br>አጠቃላይ ማደንዘዣ መጠቀም ካልቻሉ ወይም አንዳንድ የመራቢያ አካላት በሽታዎች ካሉ እነዚህን ዘዴዎች አይጠቀሙ።<br><br>መቀልበስ ከባድ ነው።<br><br>ሂደቱ በሆስፒታል ቀዶ ጥገና ክፍል ውስጥ መደረግ አለበት።<br><br>አደጋዎቹ ኢንፌክሽን፣ ደም መፍሰስ፣ ህመም እና የማደንዘዣ አለመስማማትን ያካትታሉ።<br><br>አልፎ አልፎ፣ እርግዝና ሊከሰት ይችላል። እርግዝናው ከተከሰተም፣ 30% የሚሆነው ኤክቶፒክ (ከማህፀን ውጭ) የመሆን እድል አለው።<br><br>ከሂደቱ በኋላ ህመም ሊከሰት ይችላል እና ለማገገም አንድ ወይም ሁለት ቀን ያስፈልግዎታል። | እነዚህ ዘዴዎች እርግዝናን በቋሚነት ይከላከላሉ፣ እርግዝናን በመከላከል ደግሞ በጣም ውጤታማ ናቸው።<br><br>ከቱባል ሂደቶች የበለጠ ውጤታማ እና በዋጋ ተመጣጣኝ ነው።<br><br>በሐኪሙ ቢሮ ውስጥ ሊከናወን ይችላል።<br><br>አጠቃላይ ማደንዘዣ አያስፈልግም።<br><br>ከኤችአይቪ እና ከሌሎች የአባላዘር በሽታዎች አይከላከልም።<br><br>በወንድ ብልትዎ፣ በፕሮስቴትዎ ወይም በዘር ፍሬዎ (እንደ የአባላዘር በሽታ ያለ) ወቅታዊ ኢንፌክሽን ካለብዎ ይህ ዘዴ ለእርሰዎ አይሆንም።<br><br>መቀልበስ ከባድ ነው።<br><br>ስጋቶች ኢንፌክሽን፣ ህመም እና ደም መፍሰስ ያካትታሉ።<br><br>ለመስራት እስከ 3 ወር ድረስ ይወስዳል። የዘር ፍተሻ ምርመራው ምንም አይነት የወንድ የዘር ፍሬ እንደሌለ እስከሚያሳይ ድረስ የመጠባበቂያ ዘዴን ይጠቀሙ።<br><br>ከሂደቱ በኋላ ህመም ሊከሰት ይችላል እና ለማገገም አንድ ወይም ሁለት ቀን ያስፈልግዎታል። |